7

ሰኔ 17 2012

410/0613/12

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 2
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.2

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/125 ሰኔ 11 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመውን አደጋ ለመቀነስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 29 ቀን 2012 ባካሄደው 84ኛ መደበኛ ስብሰባ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ ደንብ" መርምሮ በማጽደቅ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል መወሰኑን በመግለጽ የፀደቀውን ደንብ ልኳል፡፡

በመሆኑም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ ደንብ" የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ቅጅ 07 ገጽ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሙሌ አብዲሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
ኃላፊ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.2
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 2

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፣

ገቅ-214
15/10/12

108 63

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ገ/ፈ/1/2/125
ቀን
Date 11 ሰኔ 2012

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያጋጠመውን አደጋ ለመቀነስ በኢኮኖሚ ረገድ ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ ደንብ በመ/ቤታችን ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ የቀረበ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 29 ቀን 2012 ባካሄደው 84ኛ መደበኛ ስብሰባው በመ/ቤታችን የቀረበውን ደንብ መርምሮ በማፅደቅ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ደንቡ ሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ስለዚህ ለአፈፃፀም እንዲረዳችሁ በምክር ቤቱ የፀደቀውን ደንብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ገንዘብ ሚኒስቴር 2

ግልባጭ፣
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter Hab/GT

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

ደንብ ቁጥር _______ /፪ሺ፲፪

# የኮቪድ ፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፺፫ (፬)(ሀ) እና የኮቪድ ፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፬(፩) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወረርሽኙ ሥርጭት እያስከተለ ያለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ሰብዓዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳት ለመቀነስ እና ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን በሚያወጣቸው ደንቦች እንደሚወስን የተደነገገ በመሆኑ፣

የኮቪድ ፲፱ በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ የሚያስችሉ ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪" ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር _______/፪ሺ፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ ደንብ ዓላማ፦

፩/ "የጡረታ መዋጮ" ማለት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ አንቀጽ ፲ መሠረት በግል ድርጅቱ እና በሠራተኛው የሚደረግ መዋጮ ነው።

፪/ "ኤጀንሲ" ማለት የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው።

፫/ "አዋጅ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ (እንደተሻሻለ) ነው።

፬/ “ሚኒስቴር” ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

፭/ የኮቪድ ፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለቃላትና ሐረጎች የተሰጠው ትርጉም ለዚህም ደንብ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፫. <u>ወለድ እና መቀጫን ስለማንሳት</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ የተደነገገው ቢኖርም ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ባለው ጊዜ የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላደረገ የግል ድርጅት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ይህ ደንብ ሥራ ከዋለበት ቀን አንስቶ በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ካደረገ ሊከፍል የሚገባው መቀጫና ወለድ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

፪/ ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከመወሉ በፊት በኤጀንሲው ወይም በኤጀንሲው ውክልና በተሰጠው አካል ኦዲት ተደርጎ የሚፈለግበት የጡረታ መዋጮ ዕዳ በማስታወቂያ የተገለፀለት የግል ድርጅት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት የግል ድርጅት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ክፍሎ ካላጠናቀቀ በአዋጁ አንቀጽ 11 መሠረት መቀጫና ወለዱን እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

## ፬. <u>በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት ስለተያዘ ንብረት</u>

፩/ በጡረታ መዋጮ ዕዳ ምክንያት ሀብትና ንብረቱ የተያዘበት የግል ድርጅት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ ከከፈለ የተያዘው ንብረት ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተያዘ ንብረት ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው የግል ድርጅቱ በኢኮኖሚ ውስጥ በመንቀሳቀስ ያለ እና ንብረቱ ለሦስተኛ ወገን ካልተላለፈ ብቻ ነው፡፡

፩. <u>የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ</u>

የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የኮቪድ ፲፱ ወረርሽኝን ከመከላከል ጋር በተያያዘ ለሚያቀርቡት ዕቃ ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የሚጠየቅን የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ነፃ እንዲያደርግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፪. <u>የጊዜ ገደብን ስለማራዘም</u>

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 10(3) የተመለከተው ቢኖርም የገንዘብ ሚኒስቴር የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ባስከተለው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ያልቻሉ ላኪዎች በቫውቸር ሥርዓት ወደ አገር ያስገቡት ጥሬ ዕቃ የመጠቀሚያ የጊዜ ገደብ በአንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቀድ ይችላል፡፡

፫. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ ትክክለኛ አፈፃፀም የሚያግዝ መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡

፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከግንቦት 29 ቀን ፪ሺ፲፪ ጀምሮ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ __________ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

Ethiopian Customs Commission

REGULATION NO.___/2020

# A REGULATION ISSUED TO IMPLEMENT ECONOMIC MEASURES UNDER THE STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION ENACTED TO COUNTER AND CONTROL THE SPREAD OF COVID-19 AND MITIGATE ITS IMPACTS

**WHEREAS,** Article 93 (4) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Article 4(1) of State of Emergency Proclamation No.3/2020 Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19, provide that the Council of Ministers shall stipulate through Regulation details of the suspension of rights and measures to be taken to counter and mitigate the humanitarian, social, economic and political damages that could be caused by COVID-19;

WHEREAS, it has become necessary to take additional measures that help mitigate the economic damage that could be caused by COVID-19;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 4(1) of Proclamation No.3/2010.

## 1. Short Title

This Regulation may be cited as " State of Emergency Proclamation No. 3/2020 Implementation Council of Ministers Regulation No.______/2020"

## 2. Definitions

For purposes of this Regulation:

1) " Pension Contribution" means the pension contribution made by the private organization and the employee as provided under Article 10 of the Private Organization Employees' Pension Proclamation No. 715/2011;

2) " Agency " means the Private Organizations' Employees Social Security Agency;

3) "Proclamation" means the Private Organization Employees' Pension Proclamation No. 715/2011 (as amended);

4) " Ministry" means the Ministry of Finance.

5) Definitions provided in the State of Emergency Proclamation No.3/2020 Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 are applicable to this Regulation

ቁጥር 2
No.2
Customs Commission
Receives Document

## 3. Waiver of Penalty and Interest

1/ Notwithstanding the provisions of Article 11 of the Proclamation, Private Organizations who have not paid their Pension Contribution payable from July 8,2014 up to March 31/2020, if they pay such contribution to the Fund within 30 days from the date of issuance of this Regulation the penalty and interest accrued on such arrear shall be waived.

2/ A Private Organization audited by the Agency or by an organ authorized by the Agency and served with a notice about its pension contribution liability prior to the issuance of this Regulation may benefit from the provisions of sub-Article 1 of this Article.

3/ A Private Organization shall be liable to pay the penalty and interest imposed under Article 11 of the Proclamation if it fails to pay the Pension Contribution within the six month period provided herein.

## 4. Property Seized due to Pension Contribution Debt

1/ If a Private Organization whose property is seized due to Pension Contribution liability pays such Pension Contribution in accordance with Article 3 of this Regulation the property seized shall be returned to the owner.

2/ The property seized shall only be returned as stipulated under sub-Article 1 of this Article provided that the private organization is a going-concern and the property is not transferred to third parties.

## 5. Fees and Charges

The Ministry of Finance is hereby empowered to exempt fees and charges payable on goods and services provided by public bodies in connection with activities related to the prevention and control of COVID 19 pandemic.

## 6. Extension of Time Period

Notwithstanding the provisions of Article 10(3) of Export Duty Incentive Schemes Proclamation No. 768/2012 the Ministry of Finance may extend the period in which raw materials imported under the voucher scheme shall be used for a period of more than one year in situations where the exporter is unable to export its products due to the slowdown of the economy caused because of the corona virus pandemic.

## 7. Power to Issue Directives

The Agency is hereby empowered to issue directives for the proper implementation of this Regulation.

## 8. Effective Date

This Regulation shall be effective from 6th day of June 2020, the day it has been adopted by the Council of Ministers, through out the period the State of Emergency Proclamation remains in force.

Done at Addis Ababa this ___ day of _____ 2020.

*Abiy Ahmed (Dr.)*
*Prime Minister of the Federal Democratic*
*Republic of Ethiopia.*

Ethiopia Customs Commission
No.2